ሙስሊም የሆነ ሰው የሚናዘዘው ነገር ኑሮት ኑዛዜው እርሱ ዘንድ የተፃፈች ካልሆነች በቀር ሶስት ቀናቶችን ማደር አይገባውም።

ከኢብኑ ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁማ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: እርሱ ነቢዩን ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም - የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- እንዲህ ሲሉ ሰማ: "ሙስሊም የሆነ ሰው የሚናዘዘው ነገር ኑሮት ኑዛዜው እርሱ ዘንድ የተፃፈች ካልሆነች በቀር ሶስት ቀናቶችን ማደር አይገባውም።" ዐብደላህ ቢን ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁማ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ይህንን ሲናገሩ ከሰማው ጀምሮ ኑዛዜዬ እኔ ዘንድ የተፃፈች ሆና እንጂ አንድም ምሽት አላደርኩም።" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ሙስሊም የሆነ ሰው ትንሽ ብትሆን እንኳ አንዳች የሚናዘዘው ሐቅ ወይም ገንዘብ ኖሮ ኑዛዜው እርሱ ዘንድ የተፃፈች ካልሆነች በቀር ሶስት ቀናትን ማደር እንደማይገባው ተናገሩ። ዐብደላህ ቢን ዑመርም ረዲየሏሁ ዐንሁማ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ: " የአላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ይህንን ሲናገሩ ከሰማው ጀምሮ ኑዛዜዬ እኔ ዘንድ የተፃፈች ሆና እንጂ አንድም ምሽት አድሬ አላውቅም።"

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5831